# የቃል እምነት ኑፋቄ ዳሰሳ

2013 ዓ.ም

ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

ቅጽ 1



ወ/ም አማኑኤል እንዳለ

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

# ቅጽ አንድ

ርዕስ ፦ ሰው መንፈስ ነው ነፍስ አለው በስጋ ውስጥ ያድራል (የመጣጥፎች ስብስብ)

ጸሐፊ :- አማኑኤል እንዳለ

Gmail :- amanuelendale223@gmail.com

Facebook :- www.facebook.com/amani.love.902

Telegram :- t.me/SDG1517

Phone +251949241635

© 2013

መብቱ በሕግ የጠበቀ ነው& ያለ ጸሐፊው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ ከሥራው የተወሰነውን ክፍል ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው።

## *ምስጋና*

ከሁሉ አስቀድሜ አለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱስና ነውር አልባ እሆን ዘንድ ለመረጠኝ ከእኔ በሆነ ምንም ምክንያት ላልተደገፈ ለታላቁ ጌታ እግዚአብሔር አብ ክብርና ምስጋና ይሁን። እንዲሁም ደግሞ በበደሌና የሥጋዬን ኀጢአታዊ ባሕርይ ባለመገረዝ ሙታን ሳለሁ ደዌዬን ለተቀበለ፣ በእኔ ላይ ሊያርፍ የተገባውን ቅጣት ተሸክሞ ከራሱ ጋር ላስታረቀኝ፣ ደግሞም ከአባቱ ጋር ዘላለማዊ እርቅን ላወረደልኝ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋና ይሁንለት። የመስቀሉን እውነት በልቤ ላበራ ድንጋዩን ልቤን በሥጋ ልብ ለቀየረ ቃሉን በቅዱሳት ባሪያዎቹ በኩል ለሰጠኝ ደግሞም በቃሉ መኖርን እና መደሰትን ሁልጊዜ ለሚያድለኝ ለእርሱ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር እና ምስጋና ይሁንለት። አሜን።

በመቀጠል በዚህ የእምነት ዕቃቤ አገልግሎት እንድበረታ በተለያየ አጋጣሚ የደገፉኝ ዐርዐያ የሆኑኝ ወንድም ዘላለም መንግስቱ፣ ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ እና በሶዶ መጥመቃዊት ቤተ ክርስቲኣን መጋቢ ተስፋጺዮን አለማየሁ ጌታ እናንተን በእኔ ዘመን ሰላኖረ እግዚአብሔርን ስለመግቦቱ አመሰግናለሁ። ወንድም አማረ ታቦር (Amex) በሩቅ ሆነህ ነገር ግ በአካል የማውቅህ ያክል ወንድምነትህን የማይብህ ደግ ወንድሜ ጌታን ስላንተ አመሰግናለሁ። <<Chrstianity in Chrsis>> የሚለው የሃንግ ሃንግረፍ መጽሐፍ በብዙ ጠቅሞኛል በየዕለቱ

ለማዘጋጃቸው መጣጥፎች ዋቢ አድርጌ በዋናነት ተጠቅሜዋለሁ ይህ የአንተ ምርጡ ስጦታዬ ነው አሜክስ ወንድሜ እግዚአብሔር ጸጋን ያበዛልህ ዘንድ እመኛለሁ።

የመጨረሻው ጽሁፍ ከመልቀቁ ቀደም ብዬ የእርማት ስራውን እንዲሰራ የሰጠሁት ወንድሜ አቢኔዘር ዳንኤል ከዕረፍትህ ቆርሰህ በዚህ አገልግሎት አብረኸኝ ስለደከምክ ጌታ ያክብርልኝ።

በዚህ በስም ያልዘረዘርኳችሁ አያሌ ሰዎች አላችሁ ስማችሁን ብዘረዝር እርሱ እራሱ አንድ ሌላ መጽሐፍ ይሆንብኛል ብዬ እንጂ ግልጽ ነው። ልቤ በስም ጠርጧችኋል ከምንም በላይ ደግሞ በጌት ዘንድ ታውቃችኋል በዙሪያዬ ሰላላችሁ ደጋግ ሰዎች እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

## *ከመጽሐፉ ምን እንጠብቅ?*

ከዚህ መጽሐፍ ከአንድ የስነ መለኮት ትምህርት ቤት ምሩቅ የጻፈውን አይነት ጽሁፍ አትጠብቁ ይልቅ አንድ ለእግዚአብሔር ቃል ፍቅር ያለው ወንድሞችን በጊዜው ተንሰራፍቶ ካለ ኑፋቄ የተረዳውን ነገር በማቅረብ ቅዱሳን ይታነጹ ዘንድ አድርጋችሁ ተቀበሉ። በመጽሐፉ ውስጥ ጠንከር ያሉ የስነ መለኮት ቃላት ወይም ማብራሪያ ያላገኛችሁ እንደሆን የአንድ ለቅድስት ቤተ/ን የሚቀና ሰው ጽሁፍ ነውና ኣንደዚያ ተመልክታችሁ ልታናግሩኝ ትችላላችሁ። ጌታ በረዳኝ መጠን ጠንካራ ሙግቶችን በርዕስ ለማንሳት ሞክሬያለሁ ቀሪው እናንተ አንብባችሁ የምትሉኝ ነገር ቢሆንም ማለቴ ነው።

## አበርክቶት

በሐገራችን በዕቅብተ እምነት አገልግሎት በመትጋት ለሚያተጉን ወንድም ዘላለም መንግስቱ እና ወንድም ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ ይሁንልኝ።

## ማውጫ ገጽ


ክፍል አንድ ........ 8

መግቢያ፡- ........ 8

“የቃል እምነት መምህራን እና የሰይጣን ማታለል” ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 14

“የእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል” ........ 14

ክፍል ሦስት ........ 20

“ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው” ዮሐ 3፡6 ........ 20

ክፍል አራት ........ 29

"ይህ ስጋችን ድንኳን ነው፣ እኛ ደግሞ በድንኳን ኗሪዎች ነን" ........ 29

ክፍል አምስት ........ 37

"ፈጠረው . . . አበጀው" ........ 37

ክፍል ስድስት ........ 42

ማጠቃለያ፡- ........ 42

"ሰው ዝንጀሮም አይደለም!! ሰው አምላክም አይደለም!!" ........ 42

ዋቢ መጽሐፍት ........ 47

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

## ክፍል አንድ

***መግቢያ፦***

***"የቃል እምነት መምህራን እና የሰይጣን ማታለል"***

ይህንን ንግግር ስንሰማ ቀድሞ ወደ ልባችን የሚመጡ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ፦ ሐይሉ ዮሐንስ፥ ብስራት ብዙአየሁ (ጃፒ)፣ ቄስ ቶሎሳ ጉዲና፥ አንፍሬ አሊጋዝ እና ብዙ የቃል እምነት ምንፍቅና መምህራንን አዕምሯችን ያስታውሳል። ውሸት ተደጋግሞ ቢነገር እውነት ባይሆንም፤ ተደጋግሞ መነገሩ እና ነገሩን ደጋግመን መስማታችን ግን እንደሚጎዳን አስባለሁ። ከብዙ ጊዜ በፊት በፊልሞቻችን ሴት እና ወንድ ሲሳሳሙ እናፍር ነበር(በደጉ ጊዜ)፤ ዛሬ ግን ምንም አይመስለንም መዳራት መሆኑን ረስተን እንደ ቀላል የምናልፈው ሆኗል። ግን ይህ እንዴት ሆነ ብንል፤ ተደጋግሟላ፣ ሁሌ አየነዋ!። የቃል እምነት መምህራን ይህንን ደጋግመው ሲሉ ስንሰማ፣ በተጨማሪም ዕድሜ ለካውንስሉ ጭራሽ "ምንም ቢሆን ጴንጤ ነን እንሰብሰብና የመቃብር ቦታ ችግራችን እናስመልስ" ብለው ህብረት ጀምረዋል።

*"ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።"* ለሚለው ትምህርታቸው አያሌ ጥቅሶችን ቢጠቅሱም ቅሉ፤ ይህ ሊያስደንቀን አይገባም። ምክንያቱም ሰይጣንም ከመጀመሪያው ይህንን ያደርግ ነበርና። እግዚአብሔር በተናገረው እና ባዘዘው ውስጥ ጥርጣሬ እንዲሆንብን ያደርጋል። ጌታ ኢየሱስ በምድር በኖረበት ዘመንም *"እንዲህ ተብሎ ተጽፏል"* በማለት ጥቅስ ጠቅሶ ነበር። (የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4)

ወንድሞቼ እና እህቶቼ ልብ በሉ ሰይጣን ጥቅስ መጥቀሱ ከአሳችነት አያስቀረውም።

*<u>2ኛ ቆሮንቶስ 11 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*3 ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና*

*ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ።*

*[4] ምክንያቱም አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ እኛ ከሰበክንላችሁ ኢየሱስ*
*ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላችሁ፣ ወይም ከተቀበላችሁት መንፈስ የተለየ መንፈስ*
*ብትቀበሉ ወይም ከተቀበላችሁት ወንጌል የተለየ ወንጌል ብትቀበሉ፣*
*ነገሩን በዝምታ ታልፉታላችሁ ማለት ነው።*

…

*[14] ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን*
*መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋው ጣል።*
*[15] እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣ የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ*
*የሚያስገርም አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።*

ሰይጣን ራሱን ሊለውጥና ቅዱሳን መላዕክትን ሊመስል ይችላል፤ የእርሱን አገልጋዮች ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች ሊያስመስል ይችላል። ነገር ግን በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች የቃሉን ብርሃን የሚያበራ ቅዱሱ መንፈስ የሚያስተምር፣ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ፣ በልባችን ላይ የቃሉን ብርሃን ያበራልናል። በዚህም ሰይጣን በተንኮል ሔዋንን ካሳተበት ስህተት ራሳችንን እንድንጠብቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ይብዛልን።

ነገር ግን ሰይጣን ሔዋንን ያሳታት በምንድን ነው? ይህ በቀጥታ ወደ ዘፍጥረት የሚመራን ክፍል ነው። እስቲ ክፍሉን እንመልከት፡-

<u>*ዘፍጥረት 3 (አዲሱ መ.ት)*</u>

*[1] እባብ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከፈጠራቸው*
*የዱር አራዊት ሁሉ ተንኰለኛ ነበረ፤ ሴቲቱንም፣ “በእርግጥ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣*
*‘በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ’ ብሎአልን?” አላት።*
*[2] ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለችው፤ “በአትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት እንችላለን፤*
*[3] ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ‘በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤*

*እንዳትነኩትም፤ **አለበለዚያ ትሞታላችሁ**' ብሎአል።"*

*[4] እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ "**መሞት እንኳ አትሞቱም**፤*

*[5] ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ዐይናችሁ እንደሚከፈትና መልካምና ክፉን በማወቅ፣*

*እንደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንደምት ሆኑ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ስለሚያውቅ ነው።"*

በማድመቅ/በድምቀት ምልክት ከላይ በንፅፅር ትመለከቱ ዘንድ እንደቻላችሁት እግዚአብሔር *"ትሞታላችሁ"* ቢልም፤ ሰይጣን ግን ሔዋንን ሲያስታት አትሞቱም በማለት ነው።

ፍጹም እና ቅዱስ ከሆነው አምላክ በላይ ለፍጥረቱ የላቀ መልካምን የሚያስብ የለም፤ ነገር ግን ሰይጣን አንዳች ውሸት እንዳለ እና ቢበሉ **እንደ እግዚአብሔር** ሊሆኑ እንዳሉ ነገራቸው። *"እንደ እግዚአብሔር መሆን"* የሚለው ሀሳብ ነው ሔዋንን ያስጎመጃት ከፍሬው በስተጀርባ ያለው ውበት የታያት እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ካለ ፍላጎት የመነጨ እንጂ፣ ፍሬውን የዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እያመለከተ አትብሉ ሲልም ፍሬው ሌላ ሳይሆን የበፊቱ ፍሬ ነበር። ፍሬው አልተቀየረም።

ዛሬ እስቲ እነ ኬኔት ሄገን፣ ኬነት ኮፕላንድ የሚሉትን ፍጹም ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገር ተመልከቱ፡-

*"[Adam] was the copy, looked just like [God]. If u stood Adam upside God, they look just exactly alike. If u stood Jesus and Adam side by side, they would look and sound exactly alike" ኬኔት ኮፕላንድ*

*"Man was created on terms of equality with God, and he could stand in God's presence without any consciousness of inferiority....God has made us as much like Himeslef as possible....he made us the same class of being that he is Himself....man lived in the realm of God. He lived on terms of equal with God ..." ኬኔት ሄገን*

የሁለቱንም ሃሳብ በደንብ እንደተረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። *ኮፕላንድ* ሆነ *ሄገን* ሁለቱም አንድ ነገር ይናገራሉ አዳም የመጀመሪያው ሰው ፍጹም ከእግዚአብሔር ጋር **እኩል** ነው፤ እኩልነት ብቻ ሳይሆን *"አዳም ምንም አይነት የበታችነት ስሜት እንኳን አልነበረውም።"* ይለናል ሄገን። ነገር ግን ልብ ብለን እናስብ፤ ሰይጣን ስለምን ከሰማይ ወደ ምድር ተጣለ?

እስቲ አንድ ጊዜ ቅዱሱን መጽሐፍ እንመለከት፡-

*<u>ኢሳይያስ 14 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*12 አንተ የንጋት ልጅ፣ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፤ እንዴት ከሰማይ ወደቅ*

*አንተ ቀድሞ መንግሥታትን ያዋረድህ፤ እንዴት ወደ ምድር ተጣልህ!*

*13 በልብህም እንዲህ አልህ፤ "ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር*

*ከዋክብት በላይ ከፍ አደርጋለሁ፤ በተራራው መሰብሰቢያ፣*

*በተቀደሰውም ተራራ ከፍታ ላይ በዙፋኔ እቀመጣለሁ፤*

*14 ከደመናዎችም ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፤ ራሴንም እንደ ልዑል አደርጋለሁ።"*

*15 ነገር ግን ወደ ሲኦል፣ ወደ ጥልቁም ጕድጓድ ወርደሃል።*

ይህ ትንቢት በቀጥታ እየተነገረ ያለው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት ለሆነው ለባቢሎን ንጉስ ነው። ይህ ንጉስ እጅግ በሐብት እና በዝና የበለጠገ መሆኑን እና በሀብቱ እና በሥልጣኑ የሚመካ ንጉስ ነው። ለዚህ ንጉስ የመጣው ይህ የፍርድ ትንቢታዊ ቃል ነቢዩ ኢሳያስ ሲናገር፤ ትዕቢቱን ልክ እንደ ሰይጣን እንደሆነ እና ውጤቱም እንደዚያው እንደሆነ በመናገር ያሳያል። ታዲያ እኛ ከዚህ ምን እንማር? ሰይጣን ምንም እንኳን እንደ እግዚአብሔር መሆን ቢፈልግም፤ እግዚአብሔር ግን ከዔደን ገነት አስወጣው፤ ወደ ምድር ጣለው። ያው ሰይጣን ወደ ሔዋን መጥቶ *"ለምን ይህንን ፍሬ በልታችሁ እንደ እግዚአብሔር አትሆኑም?"* በማለት ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቃል።

ሄገን እና ኮፐላንድ ይህንን የሰይጣንን ንግግር ነው እያስተጋቡ ያሉት። ወንድሞችና እህቶቼ አንድ ነገር አስተውሉ፤ ለመሆኑ አዳም ልክ እንደ እግዚአብሔር ያለ ከሆነ፣ ከሰይጣን ንግግር ማሳቱ የቱ ጋር ነው? ዓረፍተ ነገሩን በጥንቃቄ ተመልከቱ፡-

*ዘፍጥረት 3፡4-5(አዲሱ መ.ት)*

***መሞትን*** *አትሞቱም* ***እንደ*** *እግዚአብሔር ትሆናላችሁ እንጂ።*

ሔዋን ፍሬውን ስትመለከት እውነትም ዓይኗ እንደሚከፈት እና እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆን አሰበች እንጂ ፍሬውን ስትበላ ሌላ የምትጠብቀው ውጤት አልነበራትም።

ይህ ምን ያስተምረናል? ሔዋን እንኳን እንደ እግዚአብሔር እንዳልነበረች ታውቅ ነበር፤ ነገር ግን ፍሬውን በልታ ትሆን ዘንድ ፈለገች። እናስ መጨረሻው ምን ሆነ? መጽሐፍ እንደሚል **የዘላለም ሞትን** ሞተች።

*ሮሜ 5፥12 (አዲሱ መ.ት)*

*"ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣*

*ሞትም በኀጢአት በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤*

*ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤"*

ይህ አንድ ሰውን ሰይጣን *"እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ቀላል መንገድ"* ብሎ ፍሬ ያበላውን አዳምን ያመለክታል። ታዲያ ወንድሞቼና እህቶቼ ካላችሁበት የአጋንንት ትምህርት በክርስቶስ አምናችሁ፣ እርሱም አምላካችሁ እንደሆነ አውቅችሁ፣ የዘላለም ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይሁን።

በመጨረሻም ስለ እግዚአብሔር ልናስብ እና ልናውቅ የሚገባን መሠረታዊ እውነት ከዌስትሚስተር የእምነት አንቀጽ ላቅርብና ይኼን ክፍል ላጠናቅቅ።

*1. "እውነተኛና ሕያው የሆነ አንድ አምላክ ብቻ አለ። እሱም በባሕርዩ ውስን ያልሆነና ፍጹም ብጹዕ የሆነ ንጹህ መንፈስ፡ የማይታይ ሥጋ የሌለው የማይከፋፈል ከሰዎች ባሕርይ የተለየ የማይለወጥ ታላቅ ዘላለማዊ በሰው አእምሮ ተጠቅልሎ የማይወሰን ኃያል በጥበብ የተሞላ ፍጹም ቅድስናን የተጎናጸፈ ፍጹም ነጻነት ያለው በሁሉ ነገር ፍጹም ሙሉነት የተቀዳጀ ሁሉን ነገር ለራሱ ክብር በማይለወጠውና ጻድቅ በሆነው ምክሩ የሚሠራ ፍጹም አፍቃሪ ቸር መሐሪ ታጋሽ በመልካምነትና በእውነተኝነት የበለጸገ በደልን*

*ኃጢአትንና መተላለፍን የሚምር አጥብቀው ለሚፈልጉት ዋጋቸውን የሚሰጥ በፍርዱ ፍጹም ጻድቅና አስፈሪ ኃጢአትን የሚጠላ በደለኛውን እንዲሁ ንጽሁ ነህ የማይል ነው"*

*[የዌስት ሚንስተር የእምነት መግለጫ ምዕራፍ ሁለት ትምህርተ ሥላሴ]*

በቀጣዩ ክፍል ለዚህ ሁሉ መነሻ የሆነውን *"ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።"* የሚለውን ሙግት በጌታ ጸጋ ድባቅ የምመንታ ይሆናል።

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

## ክፍል ሁለት

### *"የእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል"*

የቃል እምነት (word of faith) ትምህርት ተከታዮች ስለ ሰው ማንነት ሲያስተምሩ ሆነ ሲያምኑ *"የሰው ዋና ማንነቱ መንፈሱ ሲሆን፣ ነፍስ ያለው፣ ደግሞም በስጋ የሚኖር ነው"* ብለው ያስተምራሉ። ዓረፍተ ነገሩ በራሱ ስናነበው እንደሚሰጠን ስሜት ሰው መንፈስ ነው። ይህ መንፈስ የሆነው ሰው ደግሞ ነፍስ ያለው ደግሞም በሥጋ ውስጥ የሚኖር ነው።

ይህ ትምህርታቸውን ለመደገፍ የሚጠቀሟቸውን ምንባባት ተራ በተራ የምናይ ሲሆን፤ ከሁሉ አስቀድመን ግን አንድ ነገር በማለት እንጀምር። እኛ ወንጌላዊያን አማኞች ስለ ሰው ፍጥረት፣ ዳግም ውልደት፣ ልጅነት፣ ቅድስና፣ ቤዛነት . . . ወዘተ የቀደመ እና ጥናታዊ ትምህርቶች አሉን። ታዲያ ሰው መንፈስ አይደለም ወይም ደግሞ ሰው እንደ እግዚአብሔር ያለ አይደለም ስንል ልክ የቃል እምነት መምህራን ከንቱ ውንጀላ እንደሚያቀርቡብን ሰው በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል አልተፈጠረምም እያልን አይደለም። ወይም ደግሞ *"ከክርስቶስ ጋር አንድ ነን"* ስትሉን ምን ማለታችሁ ነው? ብለን የምንጠይቀው እኛ ከክርስቶስ ጋር አንድ ነን ወይም ከእግዚአብሔር መንፈስ ተወልደናል ብለን እናምናለን። ነገር ግን *ዳግም መወለድ ማለት ምን ማለት ነው?* የሚለው ትርጓሜ ምን እያልን እንደሆነ በቅዱሱ መጽሐፍ ብርሃን ስንመለከት ቀጥተኛ ክርስቲያን (orthodoxy chrstian) ካልሆነ ደግሞ መናፍቅ ያስብለናል።

ወደ ሃሳቤ ልመለስና የዘፍጠረቱን ምንባብ አብረን እንመልከት። የመጽሐፍ ቅዱሱ ምንባብ እንዲህ ይነበባል፡-

*ዘፍጥረት 1፣26 (አዲሱ መ.ት)*

*"እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፤*

*በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፣*

*እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ።"*

ብስራት ብዙአየሁ (ጃፒ) *"ሰው ማን ነው?"* በሚል ርዕስ ሲያስተምር፤ ሁለቱ ቃላት ማለትም *"መልክ"* እና *"አምሳል"* ላይ ትኩረት በማድረግ ለማብራራት ሞክሯል ማብራሪያውንም ሲያቀርብ እንዲህ ብሏል፡-

*"አያችሁ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል* rightly divide *ካላደረጉ እኔ ትል ነኝ ይላሉ"* በማለት ማንንም ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን ምንባብ በሌላኛው ምንባብ ለማኮሰስ ተጠቅሟል። በጃፒ አተያይ በክፍል አንድ ላይ እንዳየነው ሰው በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል ተፈጠረ ሲል በቀጥታ ወደ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ሄዶ እግዚአብሔር መንፈስ ነው ከሚለው ጋር አዛምዶ ሙግቱን ይገነባል።

እስቲ ሙግቱን ከታች እንመልከት፡-

i) ሰው በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል ተፈጥሯል ii) እግዚአብሔር መንፈስ ነው

iii) ስለዚህ ሰው መንፈስ ነው

ይህ የሙግት አወቃቀር በአመክንዮ ሕግ ደካማ ሙግት ነው። ምክንያቱም አንደኛ ወደ ድምዳሜ ሊያመጣ የቀረበው መነሻ ነጥብ እምብዛም ሐሳቡን የሚደግፍ አለመሆኑ ነው። በመከራከሪያ ነጥቦቹ ውስጥ *መልክ* እና *አምሳል* አልተተረጎሙም፤ መንፈስ የሚለውም ቃል ትርጓሜው አይታወቅም። እስቲ መንፈስ ምን ማለት እንደሆነ እንመልከትና *"መልክ"* እና *"ምሳሌ"* ምን እንደሆነ ከዘፍጥረት እንዲሁም ዮሐንስ ወንጌል ላይ እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚለውን እንመለከታለን።

1) i) መንፈስ:- (ብዙ ቁጥር ሲሆን መናፍስት ይባላል) የማይዳሰስ፣ የማይጨበጥ

ii) ረቂቅ ነገር፣ ህሊና አእምሮ፤ የመንፈስ ደስታ አገኘ

iii) ስሜት፣ ፍላጎት፤ መንፈሱ ተንሳስቷል

iv) የነገር፣ የስራ፣ የሃሳብ አዝማሚያ ሁኔታ (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አማርኛ መዝገበ ቃላት)

2) መንፈስ:- መናፍስት፣ ረቂቅ፣ የማይጨበጥ እና የማይዳሰስ፤ የማይታይ።

• እግዚአብሔር መንፈስ ነው (ዮሐ 4፥24)

• መላዕክት መናፍስት ናቸው (ዕብ 1፥7)

• ሰይጣንና ተከታዮቹ መናፍስት አጋንንትም ርኩሳት መናፍስት ይባላሉ (ማቴ 8፥16፥17 12፥28 25፥41 ሉቃ 4፥36 ይሁዳ 6)

እነዚህ ከላይ ያስቀመጥኩትን ዋቢ በማድረግ፤ *"ሰው መንፈስ ነው"* የሚለው ትርጓሜ ሊሸከም የሚገባው ሰው ረቂቅ ፍጡር ነው፣ አይታይም፣ አይዳሰስም፣ አይጨበጥም ማለት ነው። መንፈስ የሚለው ቃል የያዘው ትርጉም ይህ ከሆነ እናንተ የእምነት ቃል መምህራን ይህንን መንፈስ የሚለውን ትርጉም ምን ትሉ ይሆን?

አንድ የዚህ ስህተት ትምህርት ተከታይ *"መንፈስ እኮ ማንነት ነው"* ብሎኛል፡፡ ነገር ግን ይህ አይነት ትርጓሜ ከየት የመጣ ነው? በዚህ ትርጓሜ ውስጥ ድምዳሜያችን ምን እንደሚሆን እንመልከት፡-

i) እግዚአብሔር መንፈስ ነው

ii) ሰይጣን መንፈስ ነው

iii) ስለዚህ ሰይጣን እና እግዚአብሔር አንድ ማንነት አላቸው

ይህ ድምዳሜ እንበልና በሚለው ነው የእምነት ቃል መምህራን እና ተከታዮች ይህንን ልትጠየቁ ይገባል። ሁለተኛው ከላይ የጃፒ መነሻ አስረጂ (Permisis) ውስጥ መልክ እና አምሳል የተሸከሙት ትርጓሜ ትክክል አይደለም፡፡ እስቲ ትርጉማቸውን ቀጥለን እንመልከት፡-

መልክ = Hebrew: צֶלֶם

Transliteration: tselem

Pronunciation: tseh'-lem

ምሳሌ= Hebrew: דְּמוּת

Transliteration: dᵉmûwth

Pronunciation: dem-ooth'

እነዚህ መልክ እና ምሳሌ የሚሉት ቃላቶች ሁለት ነገርን የሚጠቁሙ ሳይሆን አንድን ነገር ለማመልከት የገቡ ቃላቶች ናቸው። צֶלֶם (tselem) ምሳሌን ወክሎ በተለያዩ ምንባባት ሲገባ፣ דְּמוּת (Demuth) ድጋሚ መልክ ለሚለው ቃል አቻ ትርጉም ሆኖ ገብቷል።

ለምሳሌ የተወሰኑ ምንባባትን እንመልከት፡-

*<u>ዘፍጥረት 5 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*[1] የአዳም የትውልድ ሐረግ እንደሚከተለው ነው፡-*

*እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን ሲፈጥረው በራሱ አምሳል አበጀው፤*

…

*[3] አዳም፣ ዕድሜው 130 ዓመት በሆነ ጊዜ፣ እርሱን ራሱን የሚመስል*

*ወንድ ልጅ ወለደ፤ ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው።*

በዚህ ምንባብ *አምሳል* እና *ራሱን የሚመስል* ልጅ አዳም እንደወለደ የሚተርከው የዘፍጥረት ምንባብ የተቀመው በዘፍ 1፥26 መልክን ወክሎ የቀረበው የዕብራይስጥ ቃል צֶלֶם (tselem)'ን ነው። ተጨማሪ ምንባባት (ዘፍ 1፥27 5፥3 ዘኍ 33፥52 1ኛ ሳሙ 6፥5 6፥11)

ነገር ግን እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንን የሚያመለክቱ ናቸው? ያለፈው ክፍል(በክፍል አንድ) ላይ ሄገን እና ኮፐላንድ *"እግዚአብሔር ራሱን በማባዛት የራሱ እኩያ ነው"* በማለት አዳምን የአምላክ ቢጤ አድርገው ነበር። ነገር ግን ሰውን ከአፈር ምራቁን እንትፍ ብሎ ካበጀ በኋላ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ብሎበታል ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ሆኗል። *መልክ* እና *አምሳል* የሚለው ቃል ትርጉም በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመተርጎም ብንሞክር በፍጹም እንደ ጃፒ እና ሌሎች የስህተት መህራን እንደሚሉት አይልም። ወዳጆቼ የእኔ ተከታይ እንድትሆኑ ሳይሆን ቃሉን በታማኝነት ትመረምሩ ዘንድ እለምናችኋለሁ። ሐሰተኛ መምህራን ዋነኛ መገለጫቸው ተከታዮችን ማፍራት ነው። በነገሮች ላይ ያለንን አስተሳሰብ እንደ ሰው ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመለከተው ይሆን ዘንድ መሆን አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ መልክ ስለሚለው ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ይላል? እስቲ አብረን እንመልከት፡-

*ኤፌሶን 4፥24 (አዲሱ መ.ት)*

*"እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን*

*እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው።"*

ይህ እግዚአብሔርን የምንመስልበት ማንነት በዳግም ልደት የተቀበልነው ረቂቅነትን ሳይሆን በኤፌሶን ምንባብ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነው።

እነርሱም፡- i) ጽድቅን እና

ii) ቅድስናን ነው።

ስለዚህ *መልክ* እና *አምሳል* የሚለው ቃል እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው ጻድቅ እና ቅዱስ አድርጎ በመፍጠሩ ነው። እስቲ አንድ ምንባብ እንጨምር፡-

*ቆላስይስ 3፥10 (አዲሱ መ.ት)*

*"የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል በዕውቀት*

*የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል፤"*

አዲሱን ልብስ ለብሰናል። ይህ አዲሱ ሰው ደግሞ በእውቀት ይታደሳል በዚህም የፈጣሪውን መልክ ይይዛል።

ከላይ ከዘረዘርነው አንድ ስንጨምር፡-

i) ጽድቅ ii) ቅድስና iii) እውቀት ናቸው ማለት ነው።

ይህም ሰው ከእንስሳ ልዩ እና በአምላኩ መልክ የመፈጠሩ ትርጉም ነው። ወደ መጨረሻ ስንመጣ የዮሐንስ ወንጌል ትርጉም ምንን ያሳየናል?

*ዮሐንስ 4፥24 (አዲሱ መ.ት)*

*"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም*

*በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል።"*

እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በመንፈስ ያመልካሉ እንጂ መንፈሶች አይደሉም፤ እግዚአብሔር ግን መንፈስ ነው። በሁሉ ስፍራ በአንድ ጊዜ ይገኛል፤ በዚህ ስፍራ እናምልክ በዚያ ስፍራ መመለክ የለበትም ሊባል አይችልም።

እግዚአብሔርን የምናመልከው፡-

i) በጽድቅ ii) በቅድስና

iii) በዕውቀት iv) በእውነት ነው

ታዲያ ከዚህ የምናገኘው ቁምነገር እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚለው ዓረፍተ ነገር፤ እግዚአብሔር ረቂቅ፣ የማይታይ፣ የማይዳሰስ፣ የማይጨበጥ መሆኑን አመላካች ነው። ስለዚህ እኛ ሕዝቦቹ *በመንፈስ* እና *በእውነት* በየትኛውም ቦታ ልናመልከው እንችላለን ማለት ነው።

በቀጣዩ ክፍል ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው የሚለውን ዮሐ 3 ምንባብ ፍታቴ እንመለከታለን።

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

## ክፍል ሦስት

### *“ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው” ዮሐ 3፥6*

በዚህ መጣጥፍ በቃል እምነት እንቅስቃሴ ኑፍቄ ላይ ዳሰሳዎቼን እየሰራሁ መሆኔ ይታወቃል። በክፍል አንድ *“ሰው መንፈስ ነው ነፍስ አለው በሥጋ ውስጥ ያድራል”* የሚለው ኑፋቄ የሰውን ማንነት ብቻ የሚገልጽ ሳይሆን፤ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በነገር ሁሉ የተካከለ እኩያ መሆኑንም የሚያሰዩበት መሆኑን *የኬኔት ሄጊንን* እና *የኬኔት ኮፐላንድን* ንግግር በመጥቀስ አሳይቼ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ኑፋቄውን ገልጬ ነበር። በክፍል ሁለት ደግሞ *“ሰው መንፈስ ነው ነፍስ አለው በሥጋ ውስጥ ያድራል”* የሚለው ንግግር የተደራጀበትን የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 26 በመመልከት የመንፈስ ምንነትን፣ እንዲሁም ይህ መንፈስ የሚለው ቃል *“ሰውን በመልካችን በአምሳላችን”* ከሚለው ገለጻ ጋር ተያይዞ እንደማይተረጎም በማየት፤ በዋናነት የቃል ኣምነት ኑፋቄ መምህር ከሆነው ብስራት ብዙአየሁ (ጃፒ) የሙግት ውቃሬ በመነሳት ትምህርቱ ምንም ያህል ከቅዱሳት መጽሐፍት ምስክርነት የተፋታ እንደሆነ አይተን ነበር።

በየክፍሉ የተነሱትን ጥያቄዎች በዘው ክፍል ለመመለስ የምሞክር ሲሆን፤ አንዳንድ ጥያቄዎች ግን ለብቻ ራሳቸውን ችለው በርዕስ ተይዞ ለመጻፍ ካሰብኩት ጋር ከተያያዘ ያንን ጊዜ አንባቢ ይጠብቀኝ ዘንድ ይሁን።

አሁን ደግሞ በቃል እምነት ኑፋቄ ከሚዘወተረው ዓረፍተ ነገር ውስጥ *“ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው”* የሚለውን ቃሉ የሚገኝበትን አውድ በጥልቀት በመመልከት ትክክለኛውን የትርጓሜ ስልት በመከተል፤ አውዳዊ ትርጉሙ በተለይ ደግሞ እውነት አሁን የቃል እምነት ተከታዮች እንደሚሉት ወንጌላዊው ዮሐንስ እያለ ይሆንን?

የክፍሉን ምባብ እንመልከት፡-

<u>*ዮሐንስ 3 (አዲሱ መ.ት)*</u>

*[1] ከፈሪሳውያን ወገን፣ ከአይሁድ አለቆች አንዱ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበረ፤*

*[2] በሌሊትም ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣ “ረቢ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ሰው በቀር*
*አንተ የምታደርጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ማንም ሊያደርግ ስለማይችል፣*
*ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር እንደሆንህ እናውቃለን” አለው።*
*[3] ኢየሱስም መልሶ፣ “እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር*
*የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” አለው።*
*[4] ኒቆዲሞስም፣ “ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል?*
*ዳግመኛ እንዲወለድ ተመልሶ ወደ እናቱ ማሕፀንስ ሊገባ ይችላልን?” አለው።*
*[5] ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር*
*ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፤*
*[6] ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው።*
*[7] ‘ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ’ ስላልሁህ አትገረም፤*
*[8] ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣*
*ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው።”*
*[9] ኒቆዲሞስም፣ “ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?” ሲል ጠየቀው።*
*[10] ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “አንተ የእስራኤል መምህር ሆነህ ሳለ እነዚህን ነገሮች አታውቅምን?*

*ቁጥር 1*

በክፍለ ምንባቡ ውስጥ በመጀመሪያው ቁጥር የጌታ ደቀ-መዝሙር ዮሐንስ አንድን ሰው ያስተዋውቀናል፤ *“ሰውዬው ስሙ **ኒቆዲሞስ** ይባላል”* በማለት ሀተታውን ይጀምራል። *“ኒቆዲሞስ የትኛው?”* ለሚል አይነት ጥያቄ ደግሞ በዛው ቁጥር *ኒቆዲሞስ* የአሁድ አለቃ በማለት ኒቆዲሞስን በደንብ ያስተዋወቀናል።

አንባቢ ሆይ! እኛ ከአህዛብ ወገን ነን፤ ለመሆኑ ፈሪሳዊያን እና የአይሁድ አለቆች ምንድናቸው? እንዲያው *“አንድ አይሁዳዊ ብሎ ብቻ ለምን አላለፈውም?”* ብለን መጠየቅ አለብን፣ ምክንያቱም የኒቆዲሞስ

መታወቂያ ስለሆነ፤ ስለ ኒቆዲሞስ ዮሐንስ የሚሰጠውን ሙሉ መገለጫ ለመረዳት ይጠቅመናልና። ይህ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በዚህ ምንባብ ይህ ሰው የተገለጸበት መንገድ በታሪኩ ውስጥ በጣም ወሳኝነት አለውና።

ፈሪሳዊያን የሚለው ቃል ከዕብራይስጥ (H6567Hebrew: פָּרַשׁ, Transliteration: pârâsh, Pronunciation: paw-rash') የተገኘ ቃል ሲሆን፤ ትርጓሜው ደግሞ የተለዩ ማለት ነው። እነዚህ የተለዩ ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ ቡድኖች በአይሁድ እምነት ውስጥ ያሉ አይሁዳዊያን ሲሆኑ፤ የሙሴ ሕግን በመጠበቅ እና በማስጠበቅ እስራኤላዊያን በባዕድ ሀገር በምርኮ (በታላቋ ሮም ቀኝ የተገዛቹበትን ጊዜ መሆኑን ልብ ይሏል) ሆነው ከአምላካቸው ሕግ እንዳይተላለፉ የሚጠብቁ እና የሚያስጠብቁ ናቸው። ምንም በምርኮ ቢሆንም የሚታደጋቸው መስፍን (መሲህ) አምላክ በገባው ተስፋ እስኪመጣ ድረስ የሙሴ ሕግ ላይ በተጨማሪም የአይሁድ አፈ-ታሪክንም በተመለከት የሚጠብቁ ቡድኖች ናቸው ፈሪሳዊያን።

ምንም እነዚህ ቡድኖች ራሳቸውን እንደዚህ ብለው ቢጠሩ እንኳን ጌታ ኢየሱስ ግን አመጸኞች እንደሆኑ እና ግብዞች በማለት የእውነትን መንገድ የሚያጣምሙ እያለ በተደጋጋሚ ይናገራል (ማቴ 23፡15 ማቴ 22፡1-15 ሉቃ 11፡52 ይነበቡ) ።

ጌታ ኢየሱስ ፈሪሳዊያንን *“ግብዞች ናቻሁ!”* ሲላቸው መልካም መስለው በሰው ዘንድ የሚታዩ መሆናቸውን እና ሰዎች እንዲያደንቋቸው፣ ድርጊታቸውን ሁሉ ለታይታ የሚያደርጉ ግን ልባቸው አመጸኛ እና ከሕጉ በተቃራኒ የሚሄዱ ግብዞች አስመሳዮች መሆናቸውን ይነግረናል።

*ቁጥር 2*

እንግዲህ ከእነዚህ ሰዎች መካከል የሆነው ኒቆዲሞስ በጠዋት ወደ ጌታ ኢየሱስ ጋር መጣ ይለናል። ታዲያ ለምን በሌሊት(በጠዋት) እንደመጣ ብዙ የመጸሐፍ ቅዱስ መምህራን ትኩረት ሰጥተው ቢያትቱም፤ እኔ ግን ከጌታ ጋር ወዳደረገው ንግግር በመሄድ ትንተናዬን ልቀጥል።

ኒቆዲሞስ ንግግሩን ሲጀምር *“መምህር ሆይ”* በማለት ነው። ኒቆዲሞስ ጌታ ኢየሱስን እንደ አንድ ታላቅ መምህር በመመልከት ከእግዚአብሔር ተልኳል፤ በዚህም ከእግዚአብሔር መላኩን ግልጽ ነው በማለት ጌታ ኢየሱስ ማን እንደሆነ እና እርሱ ስለ ጌታ ያለው ዕውቀት ምን ያህል እንደሆነ ያሳየናል። ኒቆዲሞስ ጌታ

ኢየሱስን መምህር መሆኑን ያሳመነው በእርሱ እጅ ስለተከናወኑ ተዓምራዊ ፈውሶች ናቸው። ይህ ደግሞ ከአይሁዳዊያን የሚጠበቅ ሲሆን በተለይም ደግሞ ሕጉን ከሚያጠና አንድ ፈሪሳዊ የሚጠበቅ ነው።

ለምሳሌ እግዚአብሔር ሙሴን ሲልክ ሙሴ በእግዚአብሔር ለመላኩ ማረጋገጫ ተዓምራዊ ምልክቶች አብረውት ነበሩ፤ ኢያሱ፣ ኤልያስ እና ኤልሳዕም እንደዚሁ ነበሩ። ስለዚህ እግዚአብሔር መልዕክተኛውን ሲልክ በእነዚህ ተዓምራዊ ምልክቶች የመልዕክተኛውን መልዕክት ያጸናለታል፤ ተላኪውም ደግሞ በእውነት ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ይረጋገጣል። በተመሳሳይ ይህ በጌታ ኢየሱስ እየሆነ ነውና። ኒቆዲሞስ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት ኢየሱስን እንደ አንድ ታላቅ መምህር በመመልከት አንድ ጥያቄ ያቀርብለታል። ይህ ጥያቄ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሶስት ሙሉ ሀሳብ ማብራሪያ ነው።

*ቁጥር 3*

ጌታችን ኢየሱስ በእርግጥም እውነተኛ ታላቅ መምህር ነው። ይህም እውነት ነው፤ ግን አንድ ሰው ስለጌታ ያለው እውቀት ይህ ቢሆንም እንኳን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግቢያ ቁልፉ እርሱ አይደለም።

ይህንን ቁልፍ ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ በማለት ለኒቆዲሞስ ያሳውቀዋል *"ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር"* ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ ከፈለገ የግድ ዳግመኛ መወለድ አለበት። አለበለዚያ *"የእግዚአብሔርን መንግሥት"* ማየት አይቻልም።

*ቁጥር 4*

አስተውሉ በዚህ ቦታ የተገናኙት አንደኛው ታላቅ መምህር ነው፤ ጌታም ክርስቶስ ነው:: ለመምህርነቱ ወደር የለውም። ሁለተኛው ደግሞ ኒቆዲሞስ ነው፤ ፈሪሳዊ ነው፣ ብሉይ መጽሐፍትን እያጠና የመሲሁን መምጫ የሚጠብቅ እግዚአብሔር በነቢያቱ የሰጠውን ተስፋ በመርመር ላይ ያለ። ታዲያ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ሲገናኙ ምን ዓይነት ውይይት ያደርጋሉ ብለው ይገምታሉ? መልሱ በጣም ቀላል እንደሆነ ልገምት እንዲህ ትሉ ይሆናል፡- ኦህ! በጣም የሚገርም ይሆናላ! ፍጹም በመግባባት የተዋጣለት ንግግር እንደሚያደርጉ ታስባላችሁ አይደል ? እስቲ ንባቡን እንቀጥል።

ይህንን የጌታችንን ንግግር ኒቆዲሞስ እንዴት ተረዳው? ምንስ ብሎ ተረጎመው? መቼስ የአይሁድ ታላቅ መምህር ነው፤ ለሕጉም ቀናኢ ነውና፣ ከጌታ ንግግር ጋር በመስማማት *"አዎ ይህ እኮ እንዲህ ማለትህ ነው።"* ያለው ይመስላችኋል? በፍጹም ባይሆን ኒቆዲሞስ የጌታን ንግግር ቃል በቃል (literally) በመተርጎም *"ታዲያ ጌታ ሆይ እንዴት ይሆናል ዳግመኛ ለመወለድ ሰው ከሸመገለ በኋላ ወደ እናቱ ማህጸን ገብቶ እንደገና መውጣት ነውን?"* በማለት ለጌታ ንግግር የኒቆዲሞስ መረዳት ይህ ውልደት ከስጋ ማለትም ሴት እና ወንድ በተፈጥሯዊ መንገድ በሚያልፉበት መንገድ የሚደረግ ውልደት አድርጎ ተረድቶታል። ይህም ግን ቢሆን የማይሆን እና በጣም ግራ አጋቢ ይሆንበታል። ታዲያ ምን ይሻላል? ኒቆዲሞስ ጌታ ሆይ ይህ ምን ማለት ነው? እንዴት ይሆናል በማለት ጥያቄ አቀረበ።

*ቁጥር 5*

ውድ አንባቢ ሆይ! እስካሁን ባነበብነው ምንባብ ኒቆዲሞስ ብቻ ሳይሆን እኛም ይህ የጌታ ንግግር ግር ብሎናል አይደል? ተፈጥሯዊ ሰው ይህንን እውነታ እንዴት ሊረዳው ይችላል? እኛስ የእግዚአብሔር የሆነውን እናውቅ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ይህንን እንረዳለን።

ጌታችን ቀጥሎ ባለው ቁጥር (ቁ-5) ስለ ዳግም ውልደት ለኒቆዲሞስ ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፤ በዚህኛው ቁጥር ከኒቆዲሞስ ግራ መጋባት አንጻር ጌታ ኢየሱስ የተገረመ ይመስላል። ምክንያቱም ጥያቄውን በሕጉ መጽሐፍ ውስጥ በተሰጠው የአዲስ ኪዳን ተስፋ ጋር በማጣመር ዳግም ወልደትን *"ከውሀ እና ከመንፈስ ካልተወለደ"* በማለት ይገልጸዋል። ልብ እንበል በዚህ ምንባብ ከላይ ኒቆዲሞስ ዳግም ውልደት ምንድነው ላለው ጥያቄ ኢየሱስ ማንም የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ ቢፈልግ ዳግም መወለድ አለበት(statement of fact) ላለው ንግግር በዚህ ቁጥር ደግሞ ከውሃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ የሚችል የለም ይላል። ስለዚህ ዳግም ውልደት (ቁ-3) በዚህ ምንባብ ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ ጋር በተመሳሳይ አቀረበ ።

በኢየሱስ እና በኒቆዲሞስ መካከል የሚደረገው ንግግር ውስጥ ዋናው ቁልፍ ቃል **ዳግም መወለድ** ሲሆን፤ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ለሚለው ደግሞ የጌታ መልስ የሚመስል ንግግር ሌላኛው ቁልፍ ሀሳብ ነው። በመጀመሪያ ውልደት (ከእናት እና አባት) ለመወለድ ምን ማድረግ አለብኝ? ብሎ አንድ ሰው ቢጠይቅ ፈገግ ያስብላል። ምክንያቱም እንዲህ አድርግ እንዳትሉት ከተወለደ በኋላ እንጂ ሊሰማችሁ የሚችለው

ከመወለዱ በፊት አይችልም። ከመወለድህ በፊት እናት እና አባትህን ጾታዊ ግንኙነት እንዲያደርጉ ንገራቸው ቢባል እንኳን እንዴ ሰው ሳይወለድ እንዴት ይህንን ሊያደርግ ይችላል?

ታዲያ በዳግም ውልደት ጊዜም ነገሩ እንዲያ ነው። ዳግመኛ መወለድ ውስጥ የሰው ተሳትፎ በምንም መንገድ አይኖርም። ለምን ያልን እንደሆን ሰው ራሱን መውለድ አይችልምና። ይህንን ኒቆዲሞስ የሰው ተሳትፎ ያለበት አድርጎ መረዳቱን እንዲህ በማለት ገልጾታል *"ሰው ከሸመገለ በኋላ ዳግመኛ ወደ እናቱ ማሕጸንስ መግባት አለበት ማለትህ ነው?"* ፤ በዚህ የኒቆዲሞስ ንግግር ውስጥ ሰውዬው ወደ እናቱ ማህጸን በመግባት የመጀመሪያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል ማለት ነው? እንደማለት አድርገን ብንወስድ የጌታ መልስ አይደለም ሆኖ በምንባቡ ውስጥ እናገኛለን።

*ቁጥር 6*

*ከሥጋ የተወለደ ስጋ ነው፣ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው።* በመጀመሪያው ውልደት ሰዎች ሰው ብቻ እንጂ ሌላ ምንም አይሆኑም። ባልና ሚስት ሩካቤ በመፈጸም የሚወለደው ልጅ ሰው(*ሥጋ* ብቻ) እንደሆነ ሲናገር ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው በማለት ይነግረናል። ይህ ማለት በመጀመሪያ የተወለደው ሰው አሁን በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በመወለድ መንፈስ ይሆናል ማለት ግን አይደለም። ምክንያቱም ይህ አይነት አባባል በዚህ አውድ ውስጥ መሰረታዊውን እውነት ይጣረሳል። እስቲ ቀጥለን እርሱን እንመልከት።

በዚህ ምንባብ ዳግም ውልደትን ስንረዳ ዳግመኛ መወለድ በቁጥር ሶስት ሲባል፣ በቁጥር አምስት ደግሞ ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለድክ ብሎ፤ በቁጥር ስድስት ደግሞ ከመንፈስ ካልተወለድክ ይለናል፤ ስለዚህ እነዚህ ሶስቱም አንድ አገላለጽ እንጂ የተለያዩ አይደሉም ማለት ነው። ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ ዳግመኛ መወለድ ነው፤ ዳግመኛ መወለድ የሚለው አገላለጽ ደግሞ ከመንፈስ መወለድ በሚለው ስለተጠቀሰ አንድ ነገር ናቸው።

ዳግመኛ መወለድ = ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ = ከመንፈስ መወለድ

ስለዚህ ቁጥር ስድስት ላይ ከመንፈስ መወለድ የሚልው አገላለጽ ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ የሚለውንም ሲተካ፣ ከውሃ የተወለደ ውሃ ነው ማለት ነው። ስለዚህ እኛ ዳግም የተወልድን (ከመንፈስ እና ከውሃ) መንፈስ ብቻ ሳንሆን ውሃም ነን ማለት ነው።

ግን የጽሁፉ መልዕክት እኛ መንፈስ መሆናችንን ሳይሆን **ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?** ለሚለው ለኒቆዲሞስ ጥያቄ *"ከስጋ የተወለደ ስጋ ነው፣ ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው።"* በማለት መልሶለታል። ከፍ ብሎ ባለው ምንባብ የጌታ ንግግር ቃል በቃል የሚተረጎም አለመሆኑን እናያለን። ለምን? ምክንያቱም ቃል በቃል የተረዳን እንደሆነ ልክ የኒቆዲሞስ ዓይነት ትርጓሜ እንይዛለን። ዳግመኛ መወለድ ማለት ወደ እናት ማሕጸን ድጋሚ መግባት ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ፣ ደግሞ ከውሃ እና ከመንፈስ የተወለደ ውሃ እና መንፈስ መሆን፤ ከመንፈስ መወለድ ደግሞ መንፈስ ነን ብሎ መቀበል። በመጀመሪያ ንግግሩ ጌታ ኢየሱስ ዳግም መወለድ የሚለውን ተጠቅሞ በሁለተኛው ደግሞ ከውሃ እና ከመንፈስ መወልደ በማለት ሲጠቀም እናያለን።

*ቁጥር 7*

በዚህ ሁሉ መሃል ኒቆዲሞስ መገረም (መደነቅ) ይነበብበታል። በጌታም ንግግር በጣም ግራ በመጋባት ውስጥ ሆኖ *"ይህ ሊሆን የማይችልን ነገር የሚያስተምር ምን ዓይነት መምህር ነው!" የሚል* የሚመስል መገረም ሲያሳይ እናያለን። ነገር ግን ከላይ ያለውን ሁሉ ማለትም (ከቁ 3-6) ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ የሚለው የጌታ ንግግር ዋና ዐቢይ መልዕክት ነው፤ ይህንንም በማለቱ አትገረም ይለዋል።

*ቁጥር 8*

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ለሚለው ምላሽ ሲሰጥ ደግሞ በምሳሌ ያስረዳዋል፤ ማለዳ ላይ የሚደረግ ውይይት እንደመሆኑ ነፋስ አለ ማለት ነው። *"ነፋስ ወደ ሚወደው ይነፍሳል ድምጹንም ማለትም ሽውታውን ልትሰማ ትችላለህ ነገር ግን ከዚህ ጋር መጥቶ በዛ ጋር አድርጎ ወደ እኛ መጣ አይባልም ሚቻለው አንድ ነገር ነው ነፍስ አለ ማለት ነው።"* ከመንፈስ የሚወለዱት እንደዚህ ናቸው፤ *"እንዴት ሊሆን ይችላል? ዳግም ውልደት እንዴት ነው የሚከናወነው?"* ለሚለው ጥያቄ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኋይል ዳግም ይወለዳሉ፣ መወለዳቸውም ይታወቃል፤ ያም በዳግም ውልደት በኋጥያቱ ሙት የሆነውን ሰው በመንፈስ ፍሬዎች በመባረክ፣ ፍሬ እንዲያፈሩ በመርዳት ነው፣ ፍሬያቸው ደግሞ ይታያል፤ ያ ማለት መንፈሶች ሳይሆኑ መንፈሳዊያን ሆነው ይገለጣሉ ማለት ነው።

*ቁጥር 9*

*“ኒቆዲሞስ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?”* ለዚህ ጥያቄ ከላይ ከኒቆዲሞስ ግራ መጋባት የተነሳ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ነው፡፡

*ቁጥር 10*

የጌታ ኢየሱስ መልስ ግን *“ይህንን እንዴት እስካሁን ሳታውቅ ኖረሃል? ለዛውም የአይሁድ መምህር ነህ?”* ለምን ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስ መምህር ሆኖ የእርሱን ንግግር ባለመረዳቱ ይወቅሰዋል? ምክንያቱም ይህ የአዲስ ኪዳን በረከት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሀጥያተኞችን እግዚአብሔር ዳግም በመውለድ ልጆች እንደሚያደርግ ተናግሮ ነበርና፤ ኒቆዲሞስ ግን ይህንን አያውቅም ነበር።

*“ከአሕዛብ መካከል አስወጣችኋለሁ ከየአገሩ ሁሉ እሰበስባችኋለው ወደ ገዛ ምድራችሁም መልሼ አመጣችኋለው ። ንጹህ ውሃ ረጫጭኋለው ከርኩሰትችሁ ሁሉና ከጣዖቶቻችሁ ሁሉ አነጻችኋለሁ። አዲስ ልብ እሰጣችሁለው አዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለው የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አስወግዳለው የስጋንም ልብ እሰጣችኋለው። መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድርለው ስርዐቴንም እንድትከተሉና ሕጌን እንድትጠብቁ አደርጋለው።” ት.ሕዝ 36፡24-17፣ ዘዳ 30፥6፣ ኤር 31:31-34፣ ሕዝ 11፡11-18 እና የመሳሰሉት፡፡*

ታዲያ ኒቆዲሞስ እነዚህን ምንባባት እግዚአብሔር ራሱ ውሃ በመርጨት እና አዲስን ልብ፣ አዲስን መንፈስ በውስጣቸው በማኖር ዳግም እንደሚወልዳቸው አላስተዋለውም ነበር፡፡ ስለዚህም ነበር ጌታ ኢየሱስ ይህን እንዴት አታውቅም ማለቱ።

ዳዊት ከኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህ ጋር በዝሙት ሃጥያት በወደቀ ጊዜ ሃጥያቱን በእግዚአብሔር ፊት ሲናገር አዲስ ኪዳናዊ ቋንቋን ተጠቅሟል፡፡

*<u>መዝሙረ ዳዊት 51፡2</u>*

*“በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ፣ ከሀጥያቴም አንጻኝ”*

ታዲያ መንጻት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ውልደት ሀጥያትን የሚያነጻ፣ ከእግዚአብሔር ጋርም የሚያስታርቅ መሆኑን መረዳት አለብን። እግዚአብሔር በብሉይ ምንባባት ከመንፈስ

የተወዱ መንፈሶች እንደሚመጡ ሳይሆን የተናገረው ከውሃው እና በመንፈሱ፤ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱ ሰዎችን ነው የሚያመለክተው።

*ቁጥር 11*

ከዚህም የተነሳ ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስን አንተ ይህንን አታውቅም፤ ግን መምህር ነኝ ትላለህ። እኔ ግን ይህንን አውቃለሁ ደግሞም እመሰክራለው ግን ይህንን ምስክረነታችን እናንተ አትቀበሉም፣ ምክንያቱም ደግሞ ይህንን ልትረዱ ስለማትችሉ ነው።

አጠቃላይ አውዱ ይህንን ይመስላል የምንባቡን ዋና ቃል አድርገን የወሰድነው የዳግም ውልደትን ምንነት ነው።

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

## ክፍል አራት

### "ይህ ስጋችን ድንኳን ነው፣ እኛ ደግሞ በድንኳን ኗሪዎች ነን"

በዚህ ርዕስ ላይ የቃል እምነት ኑፋቄ ዳሰሳ በሚል መጻፍ ከጀመርኩ በጌታ ጸጋ ቀናቶች አልፈዋል፤ ጌታም በብዙ እየረዳኝ ነው። እናንተም በማንበብ እና ሼር በማድረግ ነፍስን በሚደግፍ ማበረታቻ ቃላችሁ በርታ እያላችሁኝ ስላላችሁ ውድ አንባቢዎቼ ሆይ ለናንተም ያለኝ አክብሮት እና ፍቅር እንዳለ ነው። ባለፉት ተከታታይ ጽሁፎች ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆኑ በቃል እምነት ኑፋቄ ውስጥ ያሉ ወገኖችን የደረስኩ ይመስለኛል ለዚህ ምክንያት የሆነኝ ደግሞ ከዚህ ቀደም ከማውቃቸው የቃል እምነት ተከታዮች ውጪ ብዙ ሰዎች በኮሜንት እና በውስጥ መስመር እያወራሁ ስለሆነ ነው፤ በዚህም ጌታ ይመስገን።

ዛሬ ለእናንተ ይዤ የቀረብኩት ከላይ በመግቢያው የተመለከታችሁትን የቃል እምነት መምህራን የሚያቀርቡትን ሙግት ሲሆን፤ በዚህም መነሻ አድርጌ ዛሬ ክፍል አራትን የምንመለከት ይሆናል። እንደ ሁልጊዜው ይህንን ጽሁፍ አንብባችሁ ቁም ነገር ካገኛችሁ ለሌሎችም ሼር አድርጉ ካልሆነ ግን ጌታ ከዚህ በላይ ይረዳኝ ዘንድ ትጸልዩልኝ ዘንድ እለምናችኋለሁ።

በመጀመሪያ የቃል እምነት ተከታዮች የአመክንዮ ውቃሬያቸውን እንመልከታለን፤ ቀጥለን ደግሞ ይህ ሙግት የተወሰደበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምናይ ይሆናል።

ሙግት i) ይህ ስጋችን ድንኳን ተብሏል

ii) እኛ ደግሞ በድንኳን ያለን ኗሪዎች ተብለናል

iii) ስለዚህ እኛ ስጋ አይደለንም፤ አዳሪው (በስጋ ውስጥ ኗሪ) ነን። ያ ደግሞ መንፈሳችን ነው፤ ስለዚህ ሰው መንፈስ ነው!

ከላይ በቀላሉ ልትረዱት በምትችሉበት መንገድ የአመክንዮ ግንባታቸውን አቅርቢያለሁ። ይህንን ሙግት የገነቡበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንድ በአንድ እንመለከታለን።

*2ኛ ቆሮንቶስ 5 (አዲሱ መ.ት)*

*1 መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስም፣ በሰው እጅ ያልተሠራ*

*ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰማይ እንዳለን እናውቃለን።*

*2 እስከዚያው ግን የሰማዩን መኖሪያችንን ለመልበስ እየናፈቅን እንቃትታለን፤*

*3 በርግጥ ከለበስነው ራቍታችንን ሆነን አንገኝም።*

*4 በዚህ ድንኳን እስካለን ድረስ ከብዶን እንቃትታለን፤*

*ምክንያቱም ሟች የሆነው በሕይወት እንዲዋጥ ሰማያዊውን*

*መኖሪያችንን ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ አንፈልግም።*

*5 ለዚህ ዐላማ ያዘጋጀን እግዚአብሔር ነው፤ ሊመጣ ላለው ዋስትና እንዲሆነን*

*መንፈሱን መያዣ አድርጎ የሰጠንም እርሱ ነው።*

i) የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ስልቱ ብዙ ቢሆንም ማንኛውም አማኝ በጥልቀት የትርጓሜ ስልት መርሆችን ሊያስተምሩት የሚችሉትን አጋዥ መጽሐፍ ማግኘት ቢያዳግተውም፤ ቀላል መሠረታዊ ነገር ግን አለ። መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም አማኝ ሊያነበው የተገባ መጽሐፍ መሆኑ እሙን ነው። ታዲያ የምናነበውን በትክክል ለመረዳት ደግሞ አንድ መሠረታዊ ብዬ እንደ እኔ የማምነው አውድን መረዳት ነው። ይህ አውድ የምንለው በሁሉም የቋንቋ ህጎች ውስጥ አይነተኛ ሚና እንዳለው አስባለሁ።

አውድ ምንድነው? አውድ ማለት አንድ ቃል የሚገኝበት የቃል ንግግር ማለት ነው።

ለምሳሌ:- አበበ ***ሥጋዬ*** ነው።  አበበ ***ሥጋ*** ቤት።

ከበደ ***ሥጋ*** በላ።

በእነዚህ ሶስት ንግግሮች ውስጥ አንድ ስጋ የሚል ቃል ቢኖርም፤ በሶስቱም ዓረፍተ ነገር ውስጥ በውክልና የተሸከመው ቃል የተለያየ ነው። አውዱን ያልተረዳ ሰነፍ ሰው *"አበበ ስጋዬ ነው።"* ካለ በኋላ፣ *"ከበደ ስጋ በላ።"* የሚለውን ዓረፍተ ነገር ሲረዳ *"ለካ ከበደ የበላው አበበን ነው።"* በማለት የውሸት ፍርጃ እና ውንጀላ ውስጥ የሚገባ ይሆናል። ከላይ ስለ አውድ በምሳሌ ያነሳሁት ስለ አውድ ትገነዘቡ ዘንድ የደገፋችሁ ይመስለኛል።

ii) ሌላኛው ተከታይ ወሳኝ ነጥብ ደግሞ ይህንን መልዕክት ከኔ በፊት የነበሩት **ቀዳማይ ተደራሲያን** (first audience) የተረዱት እንዴት ነው? ለምሳሌ ከላይ ልንመለከት ባስቀመጥኩት ምንባብ ውስጥ የቆሮንቶስ ሰዎች *"ኦ ለካ እኛ በስጋ ውስጥ የምንኖር መንፈሶች ነን"* ብለው ይረዱ ይሆን? ብለን መጠየቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ለሰዎች ከ40 በሚበልጡ ሰዎች በኩል ለሰዎች ልጆች ሁሉ የተላከ መልዕክት ነው። መልዕክቱን በአጠቃላይ አለመረዳት ሆነ በተሳሳተ መንገድ መረዳት እጅግ በጣም ችግር ውስጥ ይከተናል፤ ጌታ ይርዳን። አሁን ወደ መጽሐፉ ምንባብ እንመለስ።

የሁለተኛ ቆሮንቶስ መጽሐፍ የተጻፈበት ምክንያት ሐዋሪያው ጳውሎስ በመጀመሪያው መልዕክቱ ውስጥ እጅግ ከክርስቲያናዊ ምግባር ባፈነገጠ አኳኋን በአህዛብ መካከል በመመላለሳቸው፣ ቤተ-ክርስቲያን ስላለችበት ሁኔታ ሰዎች ወደ ዕርሱ መጥተው እና ምን አልባትም ደግሞ ስላሉበት ሁኔታ በደብዳቤም በመግለጽ ከእርሱ ምላሽን የያዘ ነበር። በመልዕክቱም ቁጣ እና የእግዚአብሔር መንግስት ሰዎች ሊመላለሱ የሚገባቸውን የሕይወት ቱንቢ ቆፍጠን ብሎ ጽፎላቸው ነበር።

ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ ወንድሞች ምንም ይህ ቁጣ የተገባቸው ቢሆኑም፤ መለስ ብሎ ደግሞ በየዋህነት ያስብላቸዋል። በመልዕክቱ ያዘኑትን ይህንን ያደረገው ከፍቅር እና ከቁጣ ይመለሱና በክርስቲያናዊ ደስታ አብረው ይደሰቱ ዘንድ እንደሚመኝ ይገልጽላቸዋል።

<u>*2ኛ ቆሮንቶስ 2፥4 (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"እንደዚያ ስጽፍላችሁ በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት፣ በብዙም እንባ ውስጥ ነበርሁ፤*

*ይህንንም ያደረግሁት ለእናንተ ያለኝን ጽኑ ፍቅር እንድታውቁ በማለት እንጂ፣*

*እናንተን ለማሳዘን አልነበረም።"*

በሁለተኛ ቆሮንቶስ የጸሓፊውን መጋቢያዊ ልብ እያደነቅን ስንሄድ እነዚህ ቅዱሳን በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንደመሆናቸው፤ ቤተ-ክርስቲያን በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሯዊ መከራ ውስጥ የምትገኝ ሆና ሲያጽናና እና ሲያበረታቸው እንመለከታለን። ሰው ሰራሽ ያልኩት ወንድሞች በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑ ከመሆናቸው የተነሳ በኔሮ ቄሳር የሚመጣባቸውን ስደት እና መገለል ሲሆን፤ ተፈጥሯዊ ያልኩት ደግሞ በኢየሩሳሌም ያሉ ወንድሞች ደግሞ ከደረሰባቸው ድርቅ የተነሳ ነው። ወደ ምዕራፍ አራት መጨረሻ አከባቢ ስንመለከት ጳውሎስ ስለ መከራ እንዲህ ይላል፡-

*2ኛ ቆሮንቶስ 4 (አዲሱ መ.ት)*

16 *ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤ ውጫዊው ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣*

*ውስጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፤*

17 *ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል።*

18 *ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኵረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤*

*የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው።*

በቁጥር 16 እንደምንመለከተው **ውጫዊው** ሰውነታችን የሚለው ይህን ስጋችንን ነው፤ ይህ ስጋችን በአንድ ጊዜ የሚጠፋ ሳይሆን ልክ እንደ አበባ ጊዜው ሲሄድ አብሮ የሚሄድ ውበቱን የሚያጣ ነው። ለዚህም ጳውሎስ *"ውጫዊው ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣"* በማለት የሚናገረው። ነገር ግን እዚህ ጋር ማብራሪያዬን ገታ አድርጌ *"ይህ ግን ለምን ይሆናል?"* ብለን እንጠይቅ።

በመጀመሪያ ሰው ሲፈጠር ነፍሱና ስጋው ዘላለማዊ ሆነው መፈጠራቸውን ኋላ ሰው ከእግዚአብሔር ሕግ በመተላለፍ ምክንያት ሞት ወደ ሰው ልጆች ሁሉ መምጣቱን ያስተምራል (ሮሜ 5፥12) ። ታዲያ ይህ እውነታ አማኞች በዚህ በምድር እያሉስ በክርስቶስ በማመናቸው ይቀየራልን? በፍጹም አይቀየርም! ታዲያ ምን ይሆናል? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ እንዲህ ብሎ ይመልስልናል፡-

*1ኛ ቆሮንቶስ 15፥23 (አዲሱ መ.ት)*

*“ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ መጀመሪያ በኵራት የሆነው ክርስቶስ፣*

*ከዚያም በኋላ እርሱ ሲመጣ የክርስቶስ የሆኑት።”*

ሁሉም ነገር በአንዴ ሳይሆን በራሱ ተራ ይሆናል። አሁን የመንፈሳችንን ዳግም ልደት በውስጣችን ሊኖር ካለው ከመንፈስ ቅዱስ ተቀብልናል። ይቀጥልና ጳውሎስ በዚህ በውጫዊው ስጋችን ላይ የሚሆነው መከራ *“ቀላል እና ጊዜያዊ ነው”* በማለት ይነግረናል። ይህን መከራ የሚቀበለው ውጫዊው ሰውነታችን ጠፊ ነው፣ መከራው ቀላል ነው፤ ደግሞም መከራውን የምንቀበልበት ጊዜ ጥቂት ነው። ከእነዚህ ሶስቱ መጨረሻ ላይ የማይጠፋ ዘላለማዊውን ክብር እንቀበላለን።

በዚህ ምክንያት (ቁጥር 18) ዓይናችን በዚህ በሚታየው ላይ ሊሆን አይገባም፤ ይልቅ *“ያንን ዘላለማዊውን እርሱን እንመልከት”* ይለናል። ወገኖቼ ይህንን ብሎን ነው ወደ ምዕራፍ አምስት የሚወስደን። እንዴት ያለ አስደናቂ ምንባብ ነው? (ጌታ ይመስገን) በወንጌሉ እውነት ምክንያት መከራን የምትቀበሉ ደስ ይበላችሁ! እናንተ የዘላለማዊው ክብር ተስፋ ባለቤት ናችሁ። በዚህም የልባችሁን ካስማ ትከሉ።

ምዕራፍ አምስት የአራት ሃሳብ ቅጥያ ነው ነገር ግን ሀሳቡ ዘይቤያዊ አድርጎ ነው የሚቀጥለው። ምድራዊው ድንኳን (G4636Greek: σκῆνος, Transliteration: skēnos, Pronunciation: skay'-nos) ለጊዜው የሚሆን መቆያ መጠለያ ሲሆን፤ በመከራ ውስጥ ላሉ ቆሮንቶሳዊያን ይህ መልዕክት የማጽናኛ ነው። ይህ ምድራዊ ድንኳን ስጋችን በኀጢአት ምክንያት ዘላለማዊነቱን አጥቷል፣ እግዚአብሔር ለሞት ይገዛ ዘንድ አድርጎታል። ነገር ግን አማኝ ከሞት በኋላ ሕይወት ያለው ዘላለምን የሚጠባበቅ የምድር መጻተኛ ነው። በእንግድነት በሚኖርበት በዚህ ምድር መከራን በስጋው በመቀበል አለ። ይህ መከራን የሚቀበለው ውጫዊው ሰውነታችን እንጂ፤ ውስጣዊው ሰውነታችን ያንን ቀን እያሰብን የማይታየውን ዘላለማዊውን የሰው እጅ ያልሰራውን ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሚሆንልን ያንን ቤት ልናይ እንናፍቃለን።

*ለመሆኑ ይህ ቤት የምን ቤት ነው?* በዚህ ምንባብ ልንጠይቅ የሚገባ ጥያቄ ነው።

ከተወሰኑ አመታት በፊት አንድ የኮሪያ "መጋቢ" ሰማይ ቤት ደርሼ መጥቻለሁ ብሎን ነበር። ይህም ሰው ሰማይ ቤት ሰላየው ነገር ሲናገር የተለያቱ ቤቶችን እንደተመለከተ እና በመልካም ስራችን ልክ የሚገነባ ቤት ብሎን ነበር (ጌታ ምህረት ያድርግለትና)። ነገር ግን ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እያለን ያለው ቤት፣ ይህ መከራን

እየተቀበለ ባለው ስጋችን በምንቀበለው መከራ ምንም ተስፋ እንዳንቆርጥ፤ ይልቅ እግዚአብሔር በዘመን ፍጻሜ በክርስቶስ የሙታን ትንሳኤ አማኞችን ሁሉ በሚያቅፍ መሠረት አማናዊ ያደረገ የቅዱሳን ሰማያዊ እና ዘላለማዊ ቤትን እየተናገረ ነው። ይህም ቤት ልንለብስ ያለነው ሰማያው አካል እንጂ፤ ያ ሰው እንደተናገረው አይነት ቆርቆሪ ወይም ቪላ አይደለም።

ይህንን ሐሳቤን ጳውሎስ ሲያጠናክር *"ሟች የሆነው በሕይወት እንዲዋጥ"* በማለት ያስረግጣል። ይህ መጪው ተስፋ በሁለት እውነት ላይ ተቸንክሯል። አንደኛ በክርስቶስ ከሙታን በመነሳት ነው፣ ሁለተኛው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እና በመካከላችን በማደር እግዚአብሔር ለዚህ እውነት በማስረገጡ ነው። ይህ ምንባብ የሚናገረው ሊሆን ስላለው ስለ መጪው ተስፋ ሲሆን፤ አሁን በመከራ ውስጥ ላሉ ቅዱሳን ያለው ትምህርት ይህ ነው ብለን መረዳት እንችላለን።

ታዲያ ሰው መንፈስ ነው የሚል ሙግት በዚህ ክፍል እንዴት ሊገነባ ይችላል? ጳውሎስ *"ውጫዊው ሰዎችን"* በማለት ስጋችንን ከጠራ በኋላስ *"ውጫዊው ድንኳን"* ሲል ውጫዊው ሰው አይደለም እንዴት ልንል እንችላለን? ይህ አገላለጼ ለሙግት ለማመቻቸት እንጂ ሰው አንድ ሰው መንፈስ ሁለተኛ ሰው ማለቴ ሳይሆን፤ እንደው ስጋ ምንም ነው የሚለውን ትምህርት ስህተት ለማሳየት ነው።

እግዚአብሔር ሁሉ በራሱ ተራ ይሆናል ስላለን አሁን በዚህ ምድር በሁለንተናችን በቅድስና እንድንመላለስ መጽሐፍ ቅዱስ አዞናል። (1ኛ ተሰ 5፥23፤ 2 ቆሮ 7፥1)

በተመሳሳይ አገላለጽ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመከራ ውስጥ ላሉ አማኞች ይህንን ማሳሰቢያ ይሰጣል፦

<u>*2ኛ ጴጥሮስ 1 (አዲሱ መ.ት)*</u>

*12 ስለዚህ ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች ብታውቋቸውና በያዛችሁት እውነት ብትጸኑም፣*

*ስለ እነዚህ ነገሮች እናንተን ዘወትር ከማሳሰብ ቸል አልልም።*

*13 በዚህ ምድራዊ ድንኳን ውስጥ እስካለሁ ድረስ እናንተን መጐትጐት ትክክል ሆኖ ይታየኛል፤*

*[14] ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ገለጠልኝ ይህን ምድራዊ ድንኳን ቶሎ ጥዬ እንደምሄድ ዐውቃለሁ፤*

*[15] እነዚህን ነገሮች ከተለየኋችሁም በኋላ ዘወትር ታስቡ ዘንድ እተጋለሁ።*

በገዛ ክብሩና በበጎነቱ ተጠርተው በምድር ካለው ምግባረ ብልሹነት አምልጠው የተጠሩ ቅዱሳን በዚህ ክፋት ውስጥ ያሉ የአለም ሰዎች መከራ እና ስደት ያደርስባቸኋል። የክርስቲያኖች የሕይወት ምልልስ በእነዚህ አለማዊያን መካከል እንግዳ እየሆነባቸው ይሰድቧቸዋል። ይህ ብቻም አይደለም ደግሞም ሓሳዊያን መምህራንም አሉ፤ እነዚህ ዘባቾች ናቸው፣ የጌታ ዳግም መምጣት ተስፋ እና አፈ-ታሪክ ብቻ ነው የሚሉ። ስለዚህ ምክንያት ይላል ጴጥሮስ በምድራዊ ድንኳን (በስጋ) እስካለሁ ድረስ ይህንን ጉትጎታ አላቋርጥም።

ልክ እንደ ጳውሎስ አይነት ማጽናናት እና ማበረታቻ ነው ጴጥሮስም እያቀረበ ያለው። ይህንን ድንኳን (በራሱ ተራ ሊሞት ያለውን) ትቼ የምሄድበት ጊዜ ቅርብ ነው (በቅርብ በሞት ይህንን ስጋ እገላገለዋለሁ)። ነገር ግን በዚህ ሁሉ አሁንም እናንተን ማሰሰብ የምፈልገው ከቃሉ እውነት ዘር እንዳትሉ ነው።

ተደራሲያኑን ስንመለከት አንደኛ በመከራ ውስጥ ያሉ ናቸው (1ኛ ጴጥ 3፥13-16) ፤ ሁለተኛ ታላቅ የኃጢአት ግብዣ የሚቀርብላቸው ናቸው (2፥1-22) ።

ታዲያ ለእነዚህ አይነት አማኞች ጴጥሮስ ያቀረበው ሃሳብ በአጭሩ እነደዚህ ነው፡-

i) የእግዚአብሔር ፍርድ ከሰማይ ይገለጣል (2ጴጥ 2፥9-10)

ii) ምድር እና በውስጧ ያለው ሁሉ በታላቅ ትኩሳት ይጠፋል (3፥12)

iii) ሁላችንም በቅርቡ የምንሞት ነን።

ታዲያ በዚህ ምንባብ ውስጥ ጸሓፊው ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና ነጥብ ይህ ከሆነ፤ ከዚህ ውስጥ ሰው መንፈስ ነው ካልን፤ ጴጥሮስ ለምን *"ምንም እንኳን በቅርብ የሚሞቱ ቢሆንም በቅድስና እራሳቸውን ከአለማዊያን ጠብቀው"* ይኖሩ ዘንድ ያዛል? ታዲያ እኛ ከእነዚህ ምንባባት ልንረዳ የሚገባን ይህ ስጋ ጠፊ

መሆኑም ነው፤ በዚህ ጠፊ በሆነው ስጋችን ላይ በሚደርስ መከራ ተስፋ ልንቆርጥ አይገባም፡፡ ይልቅ የሰው ዐይን ያላየው፣ የሰው እጅም ያልሰራው፤ ጌታ ለሚወዱት ብሎ ያዘጋጀው ሰማያዊ ስጋን ጌታ አዘጋጅቶልናል፤ እርሱንም እስክንለብስ ድረስ በመቃተት አለን ይህም እውን የሚሆነው በጌታ መገለጥ ነውና፡፡

አይናችንን ወደ ላይ አሻቅበን አሜን ጌታ ሆይ ቶሎ ና እንላለን፤ አሜን፡፡

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በስጋ ውስጥ ያድታል።

## ክፍል አምስት

### *"ፈጠረው. . . አበጀው"*

ባለፉት በተከታታይ አራት ክፍሎች በቃል እምነት ኑፋቄ ላይ ዳሰሳ እያቀረብኩ መቆየቴ ይታወቃል። ይህ ክፍል አምስት ካለፈው የቀጠለ ሲሆን፤ በቃል እምነት መምህራን *"ፈጠረው"* እና *"አበጀው"* በሚለው ከሰው አፈጣጠር ጋር በዘፍጥረት ምንባብ የተገለጸውን እንዴት አድርገው በመጠምዘዝ ስሁት ወደ ሆነ ድምዳሜ እንደሚጓዙ እንመለከታለን፤ ከዛ በመቀጠል ደግሞ ይህን ስህተት በማረም ይህን ክፍል እንጨርሰዋለን።

የቃል እምነት መምህሩ ብስራት ብዙአየሁ (ጃፒ) *"ሰው ማን ነው?"* በሚል ርዕስ በሚያስተምር ሰዓት እነዚህን ቃላቶች እንዲህ በማለት አብራርቷል። አሰቀድመን የመጽሐፍ ቅዱሱን ምንባብ እንመልከት፡-

*<u>ዘፍጥረት 1፥27 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*"ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፤*

*በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።"*

በዚህ ቦታ ላይ ያለውን አገላለጽ ከመመልከታችን በፊት ባለፉት ምንባባት ዘፍ 1፥26 ላይ መልክ እና አምሳል በሚለው ገለጻ ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መንፈስ መሆንን ነው በማለት እንደተተረጎመ አይተን ነበር። (ክፍል ሁለት እና ክፍል ሦስትን ይጎብኙ)

አሁን ደግሞ ከዚህ በኋላ በሚመጣው ምንባብ *"እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው"* ሲል በዚህ ስፍራ የተፈጠረው *"የሰው መንፈስ ነው"* በማለት አብራርቷል መናፍቁ ጃፒ።

*<u>ዘፍጥረት 2፥7 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*"እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከምድር ዐፈር ወስዶ ሰውን አበጀው፤*

*በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ።*

በዚህ ስፍራ ደግሞ አበጀው የሚለውን ቃል በመጠቀም አስቀድሞ መንፈስን ፈጠረ ቀጥሎ ደግሞ ስጋን አበጀ በማለት ፈጠረ እና አበጀ የሚለውን ቃል ሁለት የተለያዩ ኩነቶችን እና ሁለት የተለያዩ ነገሮችን የሚያሳዩ አድርጎ አቅርቧል።

ይህንን አይነት ስህተት ለማረም ከሁሉ አስቀድመን ቃላቶቹን በደንብ ማጤን እንዲሁም ደግሞ ከተለያዩ ስነ መለኮታዊ ጥያቄዎች ጋር አቀናጅተን ብንመለከት ይህን ዓይነት ሙግት ውሃ የማያነሳ ባዶ ሙግት ሆኖ እናገኘዋለን።

ፈጠረው፡-H1254Hebrew: בָּרָא

Transliteration: bârâ’

Pronunciation: baw-raw'

ይህን ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳችን 46 የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን።

ለምሳሌ፡- ዘፍ 5፥1 6፥7 ዘኁ 16፥30 ዘዳ 4፥32 ኢያሱ 17፥15 17፥18 1ኛ ሳሙ 2፥29 እና መዝ 89 ፥47

ከላይ ባስቀመጥኩላችሁ ክፍሎች ውስጥ ፈጠረ (H1254Hebrew: בָּרָא Transliteration: bârâ’, Pronunciation: baw-raw') የሚለው ቃል ግን ጃፒ ካለው የተለየ ትርጉም ይዞ ቀርቧል። ጃፒ ከላይ ፈጠረ የሚለውን ቃል ቁስ ያልሆነን ነገር እግዚአብሔር መፍጠሩን ያሳያል ቢልም፣ የተወሰኑትን ምንባባት ስንመለከት ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኛለን፤ ቃሉ ቁሳዊ የሆነንም ኢ-ቁሳዊ የሆነን ነገርም አመላካች ሆኖ ቀርቧልና።

*ማስረጃ 1*

*<u>ኢያሱ 17፥15 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*“ኢያሱም መለሰ፣ “ቍጥራችሁ ይህን ያህል በዝቶ ኰረብታማው*

*የኤፍሬም ምድር እስከዚህ የሚጠባችሁ ከሆነ፣ ወደ ፌሪዛውያንና*

*ወደ ራፋይም ምድር ወጥታችሁ ደኑን ለራሳችሁ መንጥሩ” አላቸው።”*

ኢያሱ ሕዝቡን እየመራ ከነዓንን ከወረሱ በኋላ ለኤፍሬም የሚሆናቸውን ምድር ከሰጣቸው በኋላ፣ ምን አልባት ከጠበባችሁ ደኑን ለራሳችሁ **መንጥሩ** (ባራህ) በማለት ለራሳቸው ስፍራን እንዲሰሩ ነግሯቸዋል። ታዲያ ደንን መንጥሮ ለራስ የሚሆን ስፍራ ማዘጋጀት (ማበጀት)ወይም መፍጠር ቁስ ያልሆነን ነገር ነውን?

*ማስረጃ 2*

*<u>ኢሳይያስ 42፥5 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*“ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘረጋቸውም፣ ምድርንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ያበጀ፣*

*ለሕዝቧ እስትንፋስን፣ ለሚኖሩባትም ሕይወትን የሚሰጥ፣ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤”*

ከላይ ዘፍ 1፥27 ላይ የተጠቀመው ያንኑ ቃል በዚህ ስፍራ ሰማያትን የፈጠረ በማለት ይናገራል። ይህም የሚያሳየን ነገር ፈጠረ እና አበጀ የሚለው ቃል ሁለት የተለያዩ ነገሮችን አመላካች ሆኖ ሳይሆን አንድ ነገርን መሆኑን ያሳየናል።

አበጀ፡- Hebrew: יָצַר

Transliteration: yâtsar

Pronunciation: yaw-tsar'

*<u>ዘፍጥረት 2፥7 (አዲሱ መ.ት)</u>*

*“እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከምድር ዐፈር ወስዶ ሰውን አበጀው፤*

*በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ።”*

በዚህ ስፍራ አበጀ የሚለው ቃል በተናጠል የሰውን ስጋ መፍጠሩን እንደሚያሳይ ምንም ፍንጭ የለም። ጃፒ መጽሐፉን የግድ ጠምዝዞ ከቃሉ ወዳፈነገጠ ድምዳሜ ለመሄድ ከመፈለጉ የተነሳ ነበር። ይህ ቃል

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ 62 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ቃሉ በተገኘበት አውድ ይዞ የገባውም ትርጉም የተለያየ ነው። ለምሳሌ እነዚህን ምንባባት ይመልከቱ (2ኛ ሳሙ 17፥28 2ኛ ነገ 19፥25 1ኛ ዜና 4፥23 መዝ 33፥15 94፥9 95፥5 እና 139፥16)

አበጀ የሚለው ቃል ኢ-ቁሳዊ ለሆነም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ተሰጥቶ እናያለን።

<u>*መዝሙር 33፥15 (አዲሱ መ.ት)*</u>

*"እርሱ የሁሉን ልብ የሠራ፣ የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያስተውል ነው።"*

በዚህ ምንባብ ዳዊት ልብ በማለት የሚጠራው የሰዎች የሃሳባቸው ማዕከል በማድረግ ነው፤ ይህንንም ጌታ የሠራው ነው ይለናል። ታዲያ የሰው የሃሳብ ማዕከል ቁሳዊ እንዳይደለ ይታወቃል ሰው ምክንያታዊ ፍጥረት ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም ከአምላኩ የተቸረው ማንነት ነው። ይህንን ማንነት አበጀ ሠራ በማለት ይናገራል። እዚህ ጋር ማንሳት የፈለኩት ዋናው ነጥብ አበጀ እና ፈጠረ የሚለው ቃል የቃል እምነት መምህራን እንደሚሉት እና ስተው እንደሚያስቱን እንዳይደለ መሆኑን ነው።

በመጨረሻም ይህንን ምንባብ እንደዚህ ለሚረዱ የቃል እምነት ተከታዮች ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች የመመለስ ግዴታ አለባችሁ።

ጥያቄ፡-

i) ዘፍ 1፥27 ፈጠረ የሚለው ቃል መንፈሳችንን አመልካች ከሆነ ቀጥሎ በዛው ቁጥር ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ይላል ታዲያ ይህን ሲል መንፈስ ጾታ አለው ማለቱ ነው? ምክንያቱም በእናንተ አባባል ስጋችን ገና አልተፈጠረምና፤ ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ይኖርባችኋል።

ii) መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የተፈጠረው በስድስተኛ ቀን ነው ይለናል። ቀጥሎ በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከፍጥረት ስራ ማረፉን ይነግረናል፤ የእናንተ ትምህርት ደግሞ ይህንን ይቃረናል። ስለዚህስ ጉዳይ ምን መልስ ትሰጣላችሁ?

iii) መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ስፍራዎች የሰውን አፈጣጠር ሲናገር በአንድ ቀን የሆነ እንደሆነ ደጋግሞ ይናገራል (ዘዳ 4፥32፣ ኢሳ 45፥8) ታዲያ ይህ እንዲህ ከሆነ የሰውን አፈጣጠር በተመለከተ ዘፍ 1፥26 እና ዘፍ 2፥7 እንዴት በተለያዩ ጊዜያት የሆኑ አድርጋችሁ ተረዳችሁ?

# ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።

## ክፍል ስድስት

***ማጠቃለያ፡-***

***"ሰው ዝንጀሮም አይደለም!! ሰው አምላክም አይደለም!!"***

ያለፉት ተከታታይ ክፍሎች ላይ በቃል እምነት ኑፋቄ ላይ ስዳስስ ነበርኩ። ዳሰሳዎቼ በዋናነት በዚህ ኑፋቄ መምህራን ዘንድ የሚቀርቡ ሙግቶችን፤ እንዲሁም ደግሞ ከአውድ የተፋታ ፍታቴያቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ በመመሥረት፣ ሙግታቸውን ከተለያዩ ንጽሮቶች በመፈተሽ ደካማ ሙግት (weak argument) እንደሆኑ እና የመጽሐፍ ቅዱሱን ምንባባት ደግሞ አውዱን በተከተለ ፍታቴ ለመመለስ ጥረት አድርጌ ነበር።

በዚህ የማቀርብላችሁ ያለፉትን ሁሉ የሚጠቀልል እኛ ሰዎች ሰው እንደመሆናችን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጅ የሚያስተምረውን ትምህርት ጠቅለል ባለ መልኩ በአጭር በማቅረብ *"ሰው መንፈስ ነው፣ ነፍስ አለው፣ በሥጋ ውስጥ ያድራል።"* የሚለውን ርዕስ እቋጫለሁ።

ዛሬ እንደመደርደሪያ በማድረግ የምጀምረው የዌስትሚነስትር አጭሩ ካቴኪዝም ላይ ያለውን ጥያቄ መግቢያ አድርጌ ልውስድ

ጥያቄ 1፡- የሰው ዋና ዓላማ ምንድነው?

መልስ፡- የሰው ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ማክበር እና በእርሱም ለዘላለም መደሰት ነው።

መዝ 73፥24-26፤ ሮሜ 11፥36፤ 1ኛ ቆሮ 10፥3።

በዚህ አጭር ካቴክዝም ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች በ *"እና"* ተያይዘዋል። አንደኛ እግዚአብሔርን ማክበር፤ ሁለተኛው ደግሞ በእርሱ መደሰት ነው።

ነገር ግን ሰው *እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዴት ያውቃል?* ይህንን ጥያቄ ካልመለስን፣ የተፈጠርንበትን አላማ የማናውቅ እና በይሆናል የምንጓዝ ወይም ደግሞ ልክ ጣዖት አምላኪዎች እንደሚያደርጉት ጣዖቱ ያው ጣዖት ከመሆኑ የተነሳ እውቀት የሌለው ስለሆነ ፈቃዱን ስላልገለጠላቸው፤ የሚያመልኩት ልቅ በሆነ አስነዋሪ ምልልስ (ልቅ የሆነ ወሲባዊ እርካታ)፣ ያ ያስደስተው ይሆናል በማለት እንደሚኖሩት ለመኖር እንገደዳለን ማለት ነው። እርሱ የሰጠን መሪ ሥርዓት በብሉይና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚገኘው የእርሱ ቃል ብቻ ነው። እግዚአብሔር በቅዱሳት መጽሐፍት ፈቃዱን በመግለጡ፣ እኛ እርሱን በማክበር ለዘላለም ደስም ይለን ዘንድ በቅዱሱ መጽሐፍት ፈቃዱን መፈጸም ይገባናል። እንደ ክርስቲያን ስለ ተፈጠርነበት አላማ ስናስብ ልናስብ ከሚገባን ቀዳማዩ ይህ ነው።

ሌላኛው ደግሞ ሰው እጅግ የከበረ ፍጥረት መሆኑ ነው። በዝግመተ ለውጥ የሚያምኑ ሰዎች *"ቅድመ አያቶቻችን ዝንጀሮ ነበሩ።"* ብለው ያምናሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ ሰው ልክ እንደ እግዚአብሔር ያለ ነው በማለት ያስተምራሉ(የቃል እምነት መምህራን)። ታዲያ እነዚህ ሁለቱም የሰውን ትክክለኛ ማንነት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የቀዱት ሳይሆን፣ ተራ የሆነ ከሰው ልብ የመነጨ ከንቱ ፍልስፍና ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምንጩ ሰማያዊ ነው። ቅዱሳት ሰዎች እስቲ አሁን ደግሞ ይህንን በመጻፍ አለምን እናስደምም ብለው የደረሱት የሰው ተራ ድርሰትም አይደለም። ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ዮሐንስ ፍጹም ሕጸጽ የሌለው፣ በፍጹም ልብ ልናምነው፣ ልንታዘዘው የተገባ፣ ምስክርነቱን ልንቀበል የሚገባን መጽሐፍ ነው።

በሰው አፈጣጠር ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚነግረን ነገር ውጪ ያለ ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተጋጪ ከንቱ ረብ የሌለው ቆሻሻ እና ቆሻሻ ብቻ ነው። ስለዚህም የሰውን ማንነት መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምርበት መንገድ መቀበል ማመን፣ ይህ እግዚአብሔርን ማክበር፣ በእርሱም ለዘላለም ለመደሰት የምንችልበት ቀዳማዩ ተግባር ነው።

በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ *"ይሁን አለ"* የሚለው ቃል በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የተደጋገመ ቃል ነው። ይህ ቃል እግዚአብሔር መላ ዓለሙን (Universe) ሲፈጥር እንዴት አድርጎ እንደፈጠረ የሚያሳይ ክፍል ነው።

*ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ* (ዘፍ 1፥3)፣ *እግዚአብሔር ውሃን ከውሃ የሚለይ ጠፈር በውሆች መካከል ይሁን አለ.....እንዳለውም ሆነ* (ዘፍ 1፥7) እስከ ቁጥር 26 ድረስ ይህንን ምዕራፍ ስንሄድ *"ይሁን አለ እንዳለውም ሆነ"* የሚል ነው። በዚህ ሁሉ ግን ሰው ለነበረም ቁጥር 26 ስንደርስ ይሁን አለ ሳይሆን፤ *"እግዚአብሔርም ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንሥራ" ዘፍ 1፥26* በማለት ገና ከፍጥረት ጀምሮ *"እንፍጠር"* እና *"እንሥራ"* በማለት ነው። ሰው በቅዱስ ስላሴ *"መልክ"* እና *"አምሳል"* የተፈጠረ ይሁን የተባለ ሳይሆን፤ ታላቁ እና ፍጹም ጠቢቡ የዚህ መላ ዓለም ንድፍ አውጪ አምላክ የእጅ *ሥራ* ነው፤ ይህም የሰው ክቡር መሆንን የሚያስረዳ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን፤ ይህ ሰው የተባረከም ነው። በዘፍጥረት ምንባብ የትኛውም ፍጥረት ከዚህ ቅዱስ አምላክ ቡራኬም ሲቀበል አናይም። ሰው ግን *"ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት ግዟትም የባሕር ዓሦች የሰማይን ወፎች እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡራን ግዟቸው"* ብሎ ባረካቸው። (ዘፍ 1፥28)

ስለዚህ ሰው ክቡር ፍጡር ነው። በአምሳለ ስላሴ ተፈጥሮ፤ ደግሞም ይገዛ እና በምድር ላይ ባሉ፣ እንዲሁም በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች. . . በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን የተሰጠው፤ የታላቁ አምላክ ጌታ ባለሟል ሆኖ የተሾመ ነው። ታዲያ የቅዱሳት መጽሐፍት ምሥክርነት እውነት እና ልናምነው የተገባ ነው።

ከየትኛውም ፍጥረት በተለየ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያለው ቁርኝት በሰው ድካም ውስጥ ነው። አዳምን ከፈጠረው በኋላ የአዳምን ድካም ተመልክቶ፤ እግዚአብሔር የአዳምን ድክመት ለመሙላት፣ ሔዋንን ረዳት አድርጎ ፈጥሯል። (ዘፍ 2፥18-25) በዚህም እግዚአብሔር ሰውን ምን ያክል እንደሚወድ እና እንዳከበረም እንረዳለን።

ሌላው ሰው ክቡር መሆኑን የምንረዳው እግዚአብሔር ምንም እንኳን ታላቅ እና ፍጹም የላቀ ገናና ቢሆንም፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ ከሰው ልጅ ጋር በኪዳን ተሳስሯል። አዳምን የፈጠረበትን ሁኔታ መዝሙረኛው ሲዘምር *"በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድነው?" መዝ (8፥4)* ይህ አስገራሚ ስፍራ በመፈጠር ባገኘው በረከት ብቻ የቆመ አልነበረም። ይልቅ አዳም በመታዘዝ ይበልጥ የደስታን ሕይወት ይኖር ዘንድ

እግዚአብሔር የመታዘዝ ቃል ኪዳንን አደረገ፤ ይህ ቃል ኪዳን በሥነ መለኮት ቋንቋ *“የሥራ ቃል ኪዳን”* የምንለው ነው።

ይህ ቃል ኪዳን የሚገኘው ዘፍ 2፥15 ላይ ነው፤ ሰውን እንዲያለማትና እንዲንከባከባት በዔደን የአትክልት ስፍራ በማስቀመጥ፤ *“በአትክልት ስፍራ ከሚገኘው ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ። ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ።”* በማለት አዘዘው። ታዲያ ይህ ታላቅ አምላክ አዳም ቢታዘዝ፤ በዚህ ደስታ በፍጹም ከእግዚአብሔር ጋር ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር የገባለት ቃል ሲሆን፤ በአዳም በኩል ግን እንዳትበላ የተባለውን ባለመብላት የሚፈጸም የቃል ኪዳን በመሃላቸው ሆነ።

ነገር ግን አዳም ሊመጣ ላለው ለሰዎ ልጆች በሞላ የሚወክል ሰው ነበር፤ በእርሱ አለመታዘዝ ሞላ ዓለም የዚህ ፍርድ ተቋዳሽ ለመሆን ተገዷል። (ሮሜ 5፥12-17)

ሰው ከዚህ ክብር የወደቀበት ምክንያት ልክ ሰይጣን እንደወደቀው አይነት ምክንያት መሆኑን፤ ክፍል አንድ ላይ ተመልክተናል። ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር መሆን ፈለገ፤ ከሰማይ ወደ ምድር ተጣለ፣ ሰው እንደ እግዚአብሔር መሆንን ፈለገ፤ ሰው ከእግዚአብሔር ክብር ወጣ፣ በሁለንተናው የሞተ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ፈረደ።

ሰው ክቡር የእግዚአብሔር ፍጡር መሆኑን የምንረዳው፤ ሰውን በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር አለመተዉን ስናስተውል ነው። በዚሁ በዘፍጥረት ምንባብ ለዚህ ለወደቀው ለሰው ልጅ፤ እግዚአብሔር የመዳንን ተስፋ በሴቲቱ ዘር በኩል እንደሚያመጣ ተስፋ ሰጣቸው። (ዘፍ 3፥15-17) ይህም በሥነ መለኮት ቋንቋ *የጸጋ ቃል ኪዳን* የምንለው ነው።

ይህ የሰው ክቡር ፍጡርነት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረው ነው። በመጨረሻም ሰው ክቡር መሆኑን የምንረዳው ሁሉም ፍጥረት የሚበሰብሱ እና ከፈጣሪያቸው ስለ ወደፊቱ በቀዳማይነት ተስፋ ያልተሰጣቸው ሲሆኑ፤ የሰው ልጆች ግን በዚህ ምድር ሆነው፤ ከሞት በኋላ ሊሆን ስላለው ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገራቸው ናቸው። ሁሉም ሳይሆኑ፣ በክርስቶስ ዳግም ተወልደው፣ በእርሱ ያመኑቱ፣ ደግሞ

የመንፈስን መያዣ፤ ሊመጣ ያለውን ሕይወት ተቀብለው፤ በዚህ ምድር ፍጹም የመዳን ዋስትና (assurance of salvation) ያላቸው ሕያዋን የእርሱ የእጁ ሥራዎች ናቸው።

# ሰው ክቡር ፍጥረት ነው!!

# ቅጽ 1 ተጠናቀቀ

# ጸጋ እና ሰላም ይብዛላችሁ።

**ዋቢ መጽሐፍት**

1. Chrstianity in Chrisis, HANK HANEGRAAFF (HARVEST HOUSE PUBLISHER 1973

2. የክርስትና ትምህርቶች እና የእምነት መግለጫዎች ፣ ጥር 2007 የሉተራዊያን የእምነት መግለጫ መጽሐፍ

3. The westmiister confession of faith ቄስ ኃይሉ መኮንን "እምነታችን" ብሎ እንደ ተረጎመው (ኦርቶዶክስ ፐርስቤቴሪያን ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ ትምህርት ሥነ ጽሁፍ አገልግሎት)

4. The westminister Short Cathecism ቄስ ኃይሉ መኮንን "በጥያቄ እና መልስ መልክ የዘተጋጀ ትምህርት ብሎ እንደተረጎመው ተረጎመው (ኦርቶዶክስ ፐርስቤቴሪያን ቤተክርስቲያን የመንፈሳዊ ትምህርት ሥነ ጽሁፍ አገልግሎት)

5. The Reformed Faith_ An Exposition, Robert Shaw

6. Systematic Theology, Vicent Chung

7. Systematic Theology, By Rev. James Petigru Boyce, D. D., LL. D.,
Joseph-Emerson-Brown Professor of Systematic Theology
The Southern Baptist Theological Seminary
First published in 1887

8. Summary of Chrstian Doctrine, Louis Berkhof